## ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች

*(የጌታ ቀን—የመጀመሪያ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)*

*መልእክት ሰባት*

## ለክርስቶስ አካል እውነታ መገጣጠም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ሮሜ 12፡5፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ 12፡24፣ 31፤ 13፡1-8፤ 10፡17፤
ዘሌ. 2፡4፤ ኤፌ. 3፡16-17፤ 4፡16

**I. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛው ጫፍ የክርስቶስ አካል እውነታ ነው፤ የክርስቶስ አካል እውነታ ፍጹም ሕይወታዊ ነው—ሮሜ 8፡2፣ 6፣ 10-11፤ 12፡4-5፦**

ሀ. የሐዋርያው ጳውሎስ የማጠናቀቅ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ አካል ላይ ያተኮረ ነው—በተለይም በሮሜ፣ በ 1ኛ ቆሮንቶስ፣ በኤፌሶን እና በቆላስይስ፤ አካሉ የእግዚአብሔር ቀጣይነት ያለው ሥራ ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ ነገር ነው፣ ስለዚህ አካሉ መላው የእግዚአብሔር መገለጥ ከፍተኛው ነጥብ ነው—ሮሜ 12፡4-5፤ 1 ቆሮ. 12፡12-13፣ 18-22፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡16፤ 3፡6፤ 4፡4፣ 12፣ 15-16፤ 5፡23፣ 30፤ ቆላ. 1፡18፣ 24፤ 2፡19፤ 3፡15።

ለ. ሮሜ 12 ስለ አካሉ ከሕይወታዊ ጥምረት አንጻር ይናገራል፤ ቁጥር 5 "ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን" ይላል፦

1. ከዚህ ቁጥር ውስጥ ሁለት ቃላት ሕይወታዊውን ጥምረት ያመለክታሉ—*በ ክርስቶስ*፤ "በ ክርስቶስ" የሕይወታዊ ጥምረት ጉዳይ ነው—ተዛ. ዮሐ. 3፡16፤ ሮሜ 6፡3-6፤ 11፡17፣ 19፤ 16፡7-10፤ 1 ቆሮ. 1፡30፤ 2 ቆሮ. 2፡17፤ 5፡17፤ 12፡2፤ ገላ. 3፡27።
2. ከእርሱ ጋር ሕይወታዊ ጥምረት ያለን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ ይህ ጥምረት ከእርሱ ጋር እና ከሌሎች የአካሉ ብልቶች ጋር በሕይወት አንድ ያደርገናል፤ በዚህ ሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ ስንቆይ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ እየኖርን ነው—ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ ሮሜ 8፡4-6።
3. የክርስቶስ አካል እውን መሆን ከክርስቶስ ጋር በሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ በመቆየታችን ውስጥ ነው፤ ዮሐ. 15፡1-11 ክርስቶስ እውነተኛው የወይን ተክል እንደሆነና እኛ የእርሱ ቅርንጫፎች እንደሆንን ይገልጣል፤ እንደ የክርስቶስ ቅርንጫፎች በእርሱ መኖር አለብን፣ ይህም በቀላሉ ከክርስቶስ ጋር በሕይወታዊው ጥምረታችን ውስጥ መቆየት ማለት ነው—ቁ. 4-5፤ ተዛ. 8፡31፤ 15፡7።

**II. የጌታ ምለሳ የክርስቶስን አካል ለመገንባት ነው፤ ስለዚህ አካሉን ማወቅ ተገቢው የጌታ ምለሳ ነው—1 ቆሮ. 12፡27፤ ኤፌ. 4፡16፤ ቆላ. 3፡15፦**

ሀ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልን እንደ ሕይወታዊ ግብአቷ ትወስዳለች፤ ያለ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን ሕይወት አልባ እና የሰው ድርጅት ብቻ ትሆናለች—1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡12-13፣ 27።

ለ. አካሉ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ነው፤ ያለ አካሉ ቤተ ክርስቲያን ስሜት የማትሰጥና ትርጉም አልባ ናት—ሮሜ 12፡4-5፤ 16፡1፣ 4፣ 16።

ሐ. ፍቅር ይሸፍናል ይገነባማል፣ ስለዚህ ለክርስቶስ አካል መገንባት ማንኛውንም ነገር ለመሆንና ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ፍቅር እጅግ የላቀው መንገድ ነው—1 ቆሮ. 8፤1፤ 12፡31፤ 13፡1-8፣ 13።

መ. ሽማግሌዎች የአካሉ ሕይወት ሞዴል ለመሆን አንዳቸው ሌላቸውን በእረኝነት መንከባከብና አንዳቸው ሌላቸውን መውደድ አለባቸው፤ ሽማግሌዎች እርስ በእርስ መዋደድ አለባቸው፣ ሚስቶቻቸው እርስ በእርስ መዋደድ አለባቸው፣ አንዳቸው የሌላቸውን ልጆች መውደድ አለባቸው—ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ቆሮ. 13፡4-8።

ሠ. የአካሉ እውነታ እንዲኖረን፣ ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ቤቱን እንዲሠራ መፍቀድ አለብን፤ የአካሉ እውነታ በውስጥ የሚያድረውን ክርስቶስ በውስጥ መለማመድ ነው—ኤፌ. 3፡16-17፤ 4፡16፤ ቆላ. 1፡27፤ 3፡4፣ 15።

ረ. ጌታ የክርስቶስ አካል እውነታ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዲገለጥ በአፋጣኝ ይፈልጋል፤ ተጨባጭ የአካሉ መገለጥ ከሌለ በስተቀር ጌታ ኢየሱስ አይመለስም—ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡16፤ 5፡27፣ 30፤ ራእ. 19፡7።

ሰ. የክርስቶስን አካል ማግኘትና ጠላቱን መደምሰስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለማከናወን ጌታ ድል-ነሺዎችን ይፈልጋል፤ ያለ ድል-ነሺዎቹ የክርስቶስ አካል አይገነባም፣ የክርስቶስ አካል ካልተገነባ በቀር፣ ክርስቶስ ለሙሽራው ተመልሶ ሊመጣ አይችልም—ኤፌ. 1፡10፤ 3፡10፤ ራእ. 12፡11፤ 19፡7-9።

**III. የጌታ ምለሳ ጽዮንን—እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቁት ድል-ነሺዎቹን—ለመገንባት ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የዛሬዋ ጽዮን ላይ ለመድረስ መትጋት አለብን—ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡16፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27፤ ራእ. 14፡1፤ 21፡2፦**

ሀ. እንደ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ድምቀት እና ውበት ጽዮን የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጫፍ፣ ማዕከል፣ ከፍ መደረግ፣ መጠንከር፣ መበልጠግ፣ ውበት እና እውነታ የሆኑትን ድል-ነሺዎቹን በምሳሌ ታሳያለች—መዝ. 48፡2፣ 11-12፤ 50፡2፤ 20፡2፤ 53፡6፤ 87፡2።

ለ. ኢየሩሳሌም መላውን የቤተ ክርስቲያንን ክፍል ስታመለክት፣ ጽዮን ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ድል-ነሺዎች ታመለክታለች፤ ብሉይ ኪዳን በጽዮንና በኢየሩሳሌም መካከል ስላለው ግንኙነት በተናገረ ጊዜ ሁሉ፣ የኢየሩሳሌም መለያ ባህሪ፣ ሕይወት፣ በረከት እና መመሥረት የሚመጣው ከጽዮን እንደሆነ ያሳየናል—1 ነገ. 8፡1፤ መዝ. 51፡18፤ 102፡21፤ 128፡5፤ 135፡21፤ ኢሳ. 41፡27፤ ኢዮ. 3፡17።

ሐ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የድል-ነሺዎቹ ጥቅል-ድምር ናት፤ የጌታ አማኞች ቅሬታ፣ ቀድመው ድል-የሚነሡት፣ ለአንድ ሺህ ዓመት የጌታ ሙሽራ ይሆናሉ (ራእ. 19፡7-9፤ 20፡4-6)፤ ከዚያም ለዘላለም የክርስቶስ ሚስት ለመሆን ዘግይተው ድል-የሚነሡትን የተቀሩትን የጌታ አማኞች ይቀላቀላሉ (21፡2-3፣ 7)፦

1. በኢየሩሳሌም ውስጥ እንዳሉ የጽዮን እውነታ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ የክርስቶስ አካል እውነታ ቀድመው ድል-የሚነሡት በልባቸው ወደ ጽዮን የሚወስዱት ጎዳናዎች፤ ለመሸሸጊያቸው እንደ ጎጇቸው በናሱ መሠዊያ በተመሰለው በተሰቀለው ክርስቶስ በኩል እና ለእረፍታቸው እንደሆነ ቤታቸው በዕጣኑ መሠዊያ በተመሰለው በዕርገት ባለው ከሞት-በተነሣው ክርስቶስ በኩል እንደ መኖሪያ ስፍራቸው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ በመካተት የቤተ ክርስቲያንን መንገድ በውስጣዊ መልኩ ይወስዳሉ—መዝ. 48፡2፤ 84፡3-5፤ ተዛ. 27፡8።
2. ድል-መንሣት ማለት ጌታን ከራሳችን በላይ፣ ከነፍስ-ሕይወታችን በላይ እንወደዋለን ማለት ነው፤ ድል-ነሺ የሆነ ሰው ለክርስቶስ አካል እውነታ ክርስቶስን ብቻ ያውቃል እና ይወድዳል—ፊልጵ. 3፡10፤ 4፡12፤ ራእ.2፡4-5፣ 7፤ 12፡11።
3. የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን እርሱን መልሰው ለማምጣት እና የመንግሥቱን ዘመን ለማምጣት በትንሣኤ የክርስቶስን አካል እውነታ ይኖሩ ዘንድ ጌታ የድል-ነሺዎቹን ቡድን እየጠበቀ ነው፤ ለዚህም "ጌታ ሆይ ከአንተ ድል-ነሺዎች አንዱ እንድሆን ምህረትህንና ጸጋህን ልቀበል" ብለን መጸለይ ያስፈልገናል።

**IV. እግዚአብሔር አካልን በአንድ ላይ አገጣጠመው (1 ቆሮ. 12፡24)፤ *አገጣጠመው* የሚለው ቃል "አስተካከለ"፣ "በኅብር አደረገ"፣ "ሚዛን አስያዘ" እና "አዋሐደ" ማለት ሲሆን፣ ልዩነቶችን ማጣትን ያመለክታል፦**

ሀ. ለክርስቶስ አካል እውነታ ለመገጣጠም፣ ለክርስቶስ አካል መገንባት ክርስቶስን ወደ ሌሎች ውስጥ ለማደል በመስቀሉ በኩል ማለፍ እና በመንፈስ መሆን አለብን።

ለ. መገጣጠም ማለት ከሌሎች ጋር ኅብረት ለማድረግ ሁልጊዜ መቆም አለብን ማለት ነው፤ ከእኛ ጋር ከሚቀናጁት ሌሎች ቅዱሳን ጋር ኅብረት ሳናደርግ የትኛውንም ነገር ማድረግ የለብንም፣ ምክንያቱም ኅብረት ሚዛን ያስይዘናል፤ ኅብረት ያስተካክለናል፤ ኅብረት በኅብር ያደርገናል፤ ኅብረት ያዋሕደናል—ተዛ. ሕዝ. 1፡12 እና የግርጌ ማስታወሻ 1።

ሐ. ብዙ ጊዜ ኃላፊነትን የሚሸከሙ ወንድሞች ቡድን ያለ መገጣጠም አንድ ላይ ሊሰበሰቡ ይችላሉ፤ መገጣጠም ማለት በሌሎች እንነካለን እንዲሁም በመስቀሉ በኩል በማለፍ፣ ነገሮችን በመንፈስ በማድረግና ስለ አካሉ ስንል ሁሉን ነገር ክርስቶስን ለማደል በማድረግ ሌሎችን እየነካን ነው ማለት ነው።

መ. እንዲህ ያለው መገጣጠም ማህበራዊ ሳይሆን እያንዳንዱ ብልት፣ የዲስትሪክት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ አብሮ-ሠራተኞች እና ሽማግሌዎች የሚደሰቱት፣ የሚለማመዱት እና የሚካፈሉት ክርስቶስ መገጣጠም ነው—ተዛ. 1 ቆሮ. 1፡9።

ሠ. ቅዱሳንን ሁሉ ወደ መላው የክርስቶስ አካል የመገጣጠም ሕይወት ውስጥ ለማምጣት የሐዋርያውን ዱካ መከተል አለብን፤ የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችን በታች እንዲቀጠቅጠውና የክርስቶስን የበለጠገ ጸጋ እንድንደሰት ሐዋርያው አደራዎች በመስጠትና በሰላምታዎች ወደ መላው የክርስቶስ አካል የመገጣጠም ሕይወት ውስጥ አመጣን—ሮሜ 16፡1-16፣ 21-23፣ 20፦

1. የመገጣጠም አላማ እኛን ሁላችንን ወደ ክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ለማምጣት ነው፤ ግብ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ለመምጣት የከንውን ሂደት በሆኑት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መሆን ያስፈልገናል።

2. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በእውነት፣ በተግባራዊነትና በእርግጥ ማከናወን የሚችለው የጌታ ምለሳ ከፍተኛው ጫፍ እግዚአብሔር በቁሳዊ መንገድ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ማፍራቱ ሳይሆን የእርሱ አካል እንድትሆን ሕይወታዊ አካልን ማፍራቱ ነው።
3. ቤተ ክርስቲያን አንዱ እንጀራ የመሆኗ የጳውሎስ እሳቤ (1 ቆሮ. 10፡17) የራሱ ፈጠራ አልነበረም፤ ይልቁንም ከብሉይ ኪዳን ካለው የእህል ቁርባን የተወሰደ ነበር (ዘሌ. 2፡4)፤ የእህል ቁርባኑ ዱቄት እያንዳንዱ ክፍል ከዘይቱ ጋር ተዋሕዷል—መገጣጠም ማለት ያ ነው።
4. አንድም ሰው ስለመገጣጠም የማይናገርበት ምክንያቱ ይህ እጅግ ከፍ ያለና ጥልቅ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን እጅግ ምሥጢራዊ ስለሆነም ጭምር ነው፤ ይህ ቁሳዊ የሆነ ጉዳይ አይደለም፤ የመገጣጠማችን ትርጉም የክርስቶስ አካል እውነታ ነው።
5. መገጣጠም በበጎ ደስታው መሠረት (ኤፌ. 3፡8-10፤ 1፡9-10) እንደ እግዚአብሔር ኢኮኖሚ የመጨረሻ ግብ አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ (ራእ. 21፡2) አጽናፍ-ዓለማዊዋን የክርስቶስን አካል ለመገንባት ነው (ኤፌ. 1፡23)።

**V. የእግዚአብሔር የልቡ መሻት በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛው ጫፍ የሆነውን የክርስቶስ አካል እውነታ ለመሆን በኢየሱስ ያለው እውነታ፣ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ የተዘገበው የኢየሱስ የአምላክ-ሰው ኑሮ በእውነታ መንፈስ በብዙ የክርስቶስ አካል ብልቶች ውስጥ እንዲባዛ ነው—ኤፌ. 4፡20-24፤ 3-4፡-**

ሀ. የክርስቶስ አካል እውነታ የኢየሱስ መንፈስ የሆነው የእውነታ መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር መዋሐዱ ነው፤ የኢየሱስ መንፈስ በኢየሱስ ውስጥ ያለውን እውነታ፣ የኢየሱስን የአምላክ-ሰው ኑሮ ያካትታል—ዮሐ. 16፡13፤ ሐዋ. 16፡7፤ ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ፊልጵ. 1፡19-21።

ለ. በተዋሐደው መንፈስ ስንኖር፣ የእርሱ የሕይወት ታሪክ የኛ ታሪክ ይሆን ዘንድ በአራቱ ወንጌላት ባለው የእርሱ ሞዴል መሠረት እውነታ በኢየሱስ እንዳለ በእውነታ መንፈስ ክርስቶስን እየተማርን ነው፤ እንደ አዲሱ ሰው የክርስቶስ አካል ኑሮ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ከተገለጠው የኢየሱስ ኑሮ ጋር አንድ አይነት መሆን አለበት—ኤፌ. 1፡17፤ 2፡22፤ 3፡5፣ 16፤ 4፡23፤ 5፡18፤ 6፡18፤ ገላ. 6፡17-18፤ ሮሜ 1፡1፣ 9፤ ፊልጵ. 2፡5።

ሐ. የክርስቶስ አካል እውነታ ፍጹም በተደረጉ አምላክ-ሰዎች የሚኖር የጋራ ኑሮ ነው፣ እነርሱም ባህሪያቱ በሰናይ ባህሪያታቸው በኩል በተገለጠው በሂደት ባለፈው አምላክ ሕይወት እንጂ በራሳቸው ሕይወት የማይኖሩ እውነተኛ ሰዎች ናቸው—4፡5-9።

መ. የክርስቶስ አካል እውነታ በክርስቶስ ትንሣኤ ዳግም የተወለዱት፣ የተለወጡት እና የከበሩት ሦስት ክፍል ያላቸው አምላክ-ሰዎች ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ባለ ዘላለማዊ ጥምረት ውስጥ ያለ የመዋሐድ ኑሮ ነው—ዘሌ. 2፡4-5፤ መዝ. 92፡10፤ 1 ቆሮ. 12፡12፤ 10፡17፡-

1. *መዋሐድ* የሚለውን ቃል የምንጠቀመው ይህ ኑሮ አሁንም እየቀጠለ ስለሆነ ነው።
2. እንዲህ ያለው የመዋሐድ ኑሮ በክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ነው፣ የዚህም ትንሣኤ እውነታ መንፈስ ነው፤ ይህ ትንሣኤ የተጠናቀቀውን አምላክ ያካፍላል እንዲሁም ሞትን-ድል-ነሺውን ሕይወት ወደ አማኞች ውስጥ ይለቅቃል።

ሠ. ይህ ፍፁም በተደረጉ አምላክ ሰዎች የሚኖር የጋራ እና የመዋሐድ ኑሮ ለዘላለም እንደ እግዚአብሔር መጨመርና መገለጥ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ በሆነ መልኩ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ይጠናቀቃል—ራእ. 21፡2-3፤ 9-11፣ 22።

*© 2021 Living Stream Ministry*